# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 37 መጋቢት 26 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ


# ኮቪድ - 19 ወረርሽኝን ለመመከት እንደ ሀገር ምን እናድርግ



# ኮቪድ -19 ወረርሽኝን ለመመከት እንደ ሀገር ምን እናድርግ?

ይህ ወቅት ስለጤናችን አብዝተን የምናስብበት ጊዜ ነው፡፡ እያንዳንችን እራሳችንን ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመጠበቅ ከማንኛውም ንክኪ በኋላ አጃችንን መታጠብ አለብን፤አካላዊ ርቀትን መጠበቅ አለብን፣ አካላዊ ርቀትን መጠበቅ በማይቻልበት ሁኔታ እና ስርጭቱ የመጨመር ሁኔታ ካሳየ ከቤት አለመውጣት፣ የበሽታው ምልክቶች ማለትም ማሳል፣ትኩሳት፣ የጉሮሮ ህመም ብሎም የትንፋሽ ማጠር ስሜት ያጋጠመ እንደ ሆነ ከማንኛውም ንክኪ በማግለል ወደ ጤና ተቋም ማምራት ይኖርብናል፡፡ የበሽታውን ስርጭት ለመግታት ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ወሳኝ በመሆኑ ታማኝ የሆኑ መረጃዎችን የምናገኘው ከዓለም የጤና ድርጅት፤ከኢትዮጵያ የጤና ሚኒስተር፤ ከኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ተቋም ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡



ይህ ወረርሽኝ የዓለም ሃገራትን እና የየሃገራችንን የጤና ፖሊሲዎች ቆም ብለን እንድንፈትሽ የሚያስገድድበት ግዜ ነው፡፡ ዓለም ላይ ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅም ገንብተዋል የምንላቸው፣ የተሻለ የጤና ሥርዓት አላቸው ተብለው የሚታሰቡ ሀገራትን ወረርሽኙ እንዴት እንዳንበረከካቸው እያየን ነው፡፡ ይህ ማዕበል ስለ ጤና ያለንን አመለካከት በአትኩሮት አይተን የማኅበረሰቡን ጤና ይበልጥ ለመጠበቅ ምን ማድረግ ይኖርብናል የሚለውን በአጽንኦት እንድናስብ የሚያስገድድ ነው፡፡ የኛ ሃገር እራሷን ከዚህ ማዕበል ለመጠበቅ እያደረገች ያለችው ዝግጅት ምን መሆን ይኖርበታል እንዴትስ ማኅበረሰቡን ከዚህ ወረርሽኝ መጠበቅ ይቻላል የሚለው በአትኩሮት ሊታይ ይገባል፡፡ የኢዜማ የጤና ፖሊሲ ዝግጅት ቡድንም በዚህ ወቅት ምን ልናደርግ ይገባል የሚለውን አንደ ሚከተለው ያቀርባል፡፡

ይህን መሰል ወረርሽኞች በዓለም ላይ ሲከሰቱ የዓለም የጤና ድርጅት ኃላፊነቶችን በመውሰድ አባል ሃገራቱ ማድረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ እና መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡ ከነዚህም መካካል ወረርሽኙን እንዴት መመከት እንደሚቻል የሚያስቀምጣቸው ስልቶችና መመሪያዎች ለየሃገራቱ ከሚያደርሳቸው ግብዓቶች መካከል ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የተለያዩ ሃገራት እነዚህን ስልቶችና መመሪያዎች ከየሃገራቸው ነባር ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ጋር በማቀናጀት እንዲጠቀሙት ይመክራል፡፡ እኛም ሃገራችን ይህን መንገድ ተከትላ ምን ማድረግ ትችላለች የሚለውን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

**ሀ.** በሃገር አቀፍ ደረጃ ወረርሽኙን መግታት ስለሚቻልበት መንገድ ማቀድ፣ማስተባበር እና መከታተል

የኢትዮጵያ የጤና ሚኒስተር የየክልሉን የጤና ቢሮዎች፤ የጤናው ዘርፍ አጋዥ የሆኑ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማስተባበር ይህን ድንገተኛ ወረርሽኝ ለመመከት በቅንጅት መስራት፡፡ ቀደም ብሎ ማቀድ፤ ተግባራትን መለየት በተለይ ከሃብት አሰባበሰብ እና አጠቃቀም አንጻር ደጋፊ አካላትን በማካተት ውጤታማ ሥራ ለመሥራት መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ ይህን ከማድረግ አንጻር ሃገራችን እየሄደችበት ያለው መንገድ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ከወረርሽኙ አሳሳቢነት እና ከፍተኛ ወጪ ፈላጊነት አንጻር የሃብት አሰባሰቡ ጉዳይ ሁሉንም ማኅበረሰብ እንዲያሳትፍ ሆኖ ከዚህም በላይ ጠንክሮ መቀጠል ይኖርበታል።ወረርሽኙን ለመከላከል የትግበራ እቅዶችን ነድፎ ዝግጁነት እና አቅምን ሊያሳድጉ የሚችሉ ተግባራትን በግልጽ በማስቀመጥ በሃገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ ዝግጅት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ለ.** የመረጃ አቀራረብ እና የማኅበረሰብ ተሳትፎ

ማኅበረሰቡ ወረርሽኙን በተመለከተ ግልጽ የሆነ መረጃ እንዲኖረው በማድረግ ታማኝነትን በመገንባት ምን መደረግ ይገባዋል የሚለውን ማሳወቅ፤ በየጊዜው ያሉ መረጃዎችን በጊዜው በማድረስ ዜጎችን ዝግጁ ማድረግ፤በሃገር በቀል ቋንቋዎች ግልጽ የሆኑ ባህሉን የጠበቁ መልዕክቶችን ማስተላለፍ መቻል አለበት፡፡

በዋነኝነት የተዛቡ መረጃዎችን ማጥራት፣ አሉባልታዎችን እና የማኅበረሰቡን ስጋቶች በመለየት ወቅቱን የጠበቀ አፋጣኝ ምላሾችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የመረጃ ፍሰትን በመጠበቅ እና የተዛቡ መረጃዎችን ከማጥራት አንጻር በአሁኑ ወቅት በሃገራችን እየተሠራ ያለውሥራ ብዙ ክፍተቶች ያሉበት ነው፡፡ይህም በጥንቃቄ ሊታሰብበት የሚገባ እና ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

**ሐ.** ተጋላጮችን ከመለየት አንጻር ጽኑ ክትትል እና የመለየት ሥራን ማጠናከር

ቅድመ መለየት ሥራን ስናከናውን ችግሩ የታየባቸውን ቦታቸውን መለየት የስርጭቱን መጠን እና ጥንካሬ እንዲሁም ባህሪ ማወቅ በጤና ሥርዓቱ ላይ እያስከተለ ያለውን ጫና ለመቀነስ እንዲረዳ ቅደም ተከተሎችን በማስቀመጥ ይበልጥ አትኩሮት የሚሹትን መለየት ከዚህ ጋር ተያይዞ የተገኙ ተጠቂዎችን መለየት እና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ በጥንቃቄ ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች ናቸው፡፡ ይህን ከማድረግ አንጻር ሰፊ ሥራ እየተሠራ ቢገኝም እነዚህን ግኝቶች ለማኅበረሰቡ ማሳወቅ ላይ ግን ችግሮች ይታያሉ፡፡ይህን ክፍተት በፍጥንነት ፈትቶ ማኅበረሰቡን ማንቃት ስርጭቱን ለመግታት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

**መ.** የወረርሽኙ መግቢያ መንገዶችን መለየት

የየብስ ድንበሮችን በአየር በረራ የሚመጡ መንገደኞችን ኅብረተሰቡን ተቀላቅለው ስርጭቱን እንዳያስፋፉት መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ከማድረግ አንጻር መንግሥት እየሄደበት ያለው መንገድ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡

**ሠ.** ሃገር አቀፍ የናሙና መመርመሪያ ተቋማትን ማዘጋጀት

ዓለም አቀፉን የጤና ድርጅት እንዲሁም ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ያሉንን የናሙና መመርመሪያ አቅሞችን ማሳደግ፤ በስፋት መመርመር የወረርሽኙን ስርጭት ከመግታት አንጻር ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የመመርመር አቅምን ከማሳደግ አንጻር በአትኩሮት መሥራት፡፡ የናሙና መመሪያ ተቋማትን ከማዘጋጀት እና ከማስፋት አንጻር ብርቱ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም በተቻለ መጠን ከዚህም በላይ መሆን የሚችሉበትን አቅም ለመፍጠር መንቀሳቀስ፡፡

**ረ.** በጤና ተቋማት ውስጥ ኢንፌክሽኖችን ሰለመከላከል

የኢንፌክሽን መከላከል እና ቁጥጥር አሠራርን ማጠናከር የበሽታውን መተላለፍ መጠን ከሚወስኑት ተግባራት ዋነኛው ተግባር መሆኑ ይታወቃል እና በዚህ ወረርሽኝ የተጠቁ ታማሚዎችን የሚንከባከቡ እና ህክምና የሚሰጡ ባለሙያዎችን ጤንነት ከመጠበቅ አንጻር ሃገር አቀፍ ዝግጅቶችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተላላፊነትን ለመመከት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በሚገባ ማቅረብ ጤና ባለሙያዎች ጤንነታቸው ተጠብቆ እንዲሠሩ አቅርቦትን ከፍ ማድረግ ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊሠራ የሚገባ ሥራ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት እንደ ሀገር እየተደረገ ያለው ጥረት የሚታይ ቢሆንም ውጤታማ እንዲሆን በይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያስፈልጋል፡፡

**ሸ.** ወረርሽኙን ለመመከት መሥራት

የጤና ተቋማት ማዘጋጀት አዳዲሶችን መጨመር፤ባለሙያዎችን ማሠልጠን፤ ታማሚዎችን የመለየት እና ቅደም ተከተል የማውጣት ሥራ መሥራት፤ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ተጠቂዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው በማሳወቅ እራሳቸውን የሚረዱበትን መንገድ ማመቻቸት፤ የተለየ አትኩሮት የሚፈልጉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በመለየት ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ማድረግ ዋና ዋና ተግባራት ሲሆኑ በሃገር አቀፍ ደረጃ በጥሩ ሁኔታ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች በመሆናቸው ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡በተለይ ይህ ወረርሽኝ ተስፋፊነቱ የመጨመር አድል ካገኘ በመቀጠል ልንሠራቸው ከሚያስፈልጉ ሥራዎች አንዱ ሁሉን ነገር ዘግቶ መቀመጥ ሊሆን ከቻለ ይህን ተያይዞ ለሚመጡ ማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና የደህንነት ስጋቶችን ከአሁኑ መዝኖ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ቀ.** አቅርቦት እና ድጋፍ

በሃገር አቀፍ ደረጃ ያሉ አቅርቦቶችን ማወቅ ተጨማሪ የህክምና ቁሳቁሶችን እና የመድሃኒት አቅርቦቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያሉንን ሃብቶች በማሰባሰብ ሙሉ አቅማችንን ይህን ወረርሽኝ መመከት ላይ ማሳረፍ ያስፈልጋል፡፡ መንግሥት ማኅበረሰቡን በማሳተፍ ሃብቶችን ማሰባሰብ ላይ እየሠራ ያለው ጠንካራ ሥራ አሳታፊ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡

በአጠቃላይ ይህን ወረርሽኝ ከመመከት አንጻር እንደሀገር እየተሠራ ያለውሥራ ውጤታማ እንዲሆን ባለን አቅም መሥራት የምንችላቸውን ዋና ዋና ተግባራት መለየት፤ ያለንን አቅም ከፍ ለማድረግ ያሉብንን ጉድለቶች እንዴት እናጠነክራለን የሚለውን መለየት እናም በስፋት ለመሥራት የሚያስችለንን እቅድ መንደፍ እና መተግበር፤ በመጨረሻም የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓትን በመዘርጋት አፈጻፀሙን በሚገባ መገምገም ያስፈልጋል፤እነዚህ ተግባራትን እውን ለማድረግ አሳታፊነት ላይ በርትቶ መሥራት ያስፈልጋል ሁሉንም ያሳተፈ እንቅስቃሴ የባለቤትነትን ስሜት ስለሚፈጥር በተባበረ ክንድ ይህን አስቸጋሪ ጊዜ ለማለፍ ይረዳል፡፡ በተለይ ከመረጃ ስርጭት እና ፍሰት አንጻር ያሉትን ችግሮች በመፍታት ማኅበረሰቡ ላይ ያሉ የተዛቡ መረጃዎች እና ጥርጣሬዎችን ማጽዳት ለነገ የማይተው ሥራ መሆን አለበት።


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

መጋቢት 26 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ቅኝት

## < <የአካባቢው ነዋሪ በመረጠውና በፈለገው ሰው የመተዳደር መብቱ እንዲጠበቅለት እንሰራለን> >

በዛሬው የቅኝት አምዳችን ከአዲስ አበባ ወጥተን ወደ ወላይታ ዞን ነው የምንጓዘው፡፡ በወላይታ ዞን ከሚገኙ የምርጫ ወረዳዎች መሀል በአደረጃጀቱ ጠንካራ ከሆነው ምርጫ ወረዳ መሀል አንዱን መርጠን እንቃኛለን፡፡ በወላይታ ዞን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በ8 ምርጫ ወረዳዎች አደረጃጀቱን ዘርግቷል፡፡ የዛሬው የቅኝት አምድ ከ8ቱ መሀል አንዱን የምርጫ ወረዳ ብቻ የምንቃኝበት ነው፡፡ የሚቃኘው የምርጫ ወረዳ በወላይታ ዞን‹‹ገሱባ››ከተማ ውስጥ የሚገኘው የጉፋ ምርጫ ወረዳ ነው፡፡ የጉፋ ምርጫ ወረዳን በስሩ ለመዳሰስ




ሙከራ ባደረግንበት በዚህ አጭር ጽሑፍ ላይ የምርጫ ወረዳው ሰብሳቢ ላደረሱን መረጃ በአንባቢዎቻችን ስም እናመሰግናለን፡፡

### የጉፋ ምርጫ ወረዳ መቸ ተቋቋመ ምን ያሕል አባላትንስ አቅፏል?

የጉፋ ምርጫ ወረዳ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከመመስረቱ በፊት አርበኞች ግንቦት7 ወደ ሀገር ቤት በገባ ማግስት በጊዜያዊነት የተመሰረተ ሲሆን አርበኞች ግንቦት7 ከስሞ ኢዜማ ሲመሰረት ይህ መዋቅርም ተጠቅልሎ ወደ ኢዜማ እንዲገባ መደረጉንና በገሱባ ከተማ የሚገኘው የምርጫ ወረዳው ዋና ቢሮም የኢዜማ ቢሮ ሆኖ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ኢዜማ ከተመሰረተ በኋላ በተካሄደ ጠቅላላ ጉባኤም ምርጫ ወረዳው እንደ አዲስ ሥራአ ስፈፃሚ አባላቱን በጠቅላላ ጉባኤው በማስመረጥ ወደ ሥራገብቷል፡፡ ሥራ አስፈፃሚው ከተዋቀረ በኋላም ምርጫ ወረዳው 256 ያሕል አባላትን በአባልነት መዝግቦ ይዟል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 38 ያሕሉ ሴቶች መሆናቸውን የምርጫ ወረዳው ሰብሳቢ ይገልፃሉ፡፡

### የምርጫ ወረዳው አደረጃጀት ምን ይመስላል?

በወላይታ ዞን ሥር የሚገኘው የጉፋ ምርጫ ወረዳ በሥሩ 34 ቀበሌዎችን አቅፎ ይዟል፡፡ በምርጫ ወረዳው ሥር 90 የምርጫ ጣቢያዎች አሉ፡፡ የወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ ሥራ አስፈፃሚ አባላትን ከመረጠ በኋላ በ34ቱም ቀበሌዎች አደረጃጀት ለመዘርጋት መሞከሩን የምርጫ ወረዳው ሰብሳቢ ያስረዳሉ፡፡ በእቅድ ደረጃ ይዘውት▶



▶ ከነበረው በ34ቱም ቀበሌዎች አደረጃጀት የመዘርጋት እቅዳቸው መሀል በ25ቱ ቀበሌዎች የተሳካ አደረጃጀት ለመፍጠር መቻሉን ሰብሳቢው ይገልፃሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከ34ቱ ቀበሌዎች መሀል በ25ቱ ቀበሌዎች የተሟላ ሥራ አስፈፃሚ መመደብ ተችሏል፡፡ በየቀበሌው የተመረጡ ሥራ አስፈፃሚ አባላትም በየቀበሌው ለሚገኘው ነዋሪ ስለ ኢዜማ ግንዛቤ እንዲኖረው ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መሥራት መቻላቸውን ሰብሳቢው ጠቁመዋል፡፡ በየቀበሌው የኢዜማ ራዕይና ተልዕኮን በቀበሌ ሥራ አስፈፃሚዎች በኩል ለሕዝብ የማዳረስ ሥራ መሠራቱን ሰብሳቢው ይገልፃሉ፡፡ በየቀበሌው የኢዜማ ቢሮ ለማደራጀት ሙከራ መደረጉንና ከ34ቱ ቀበሌዎች መሀል በ10ሩ ቀበሌዎች ቢሮ መክፈት መቻሉን ሰብሳቢው ይናገራሉ፡፡ ሁሉንም ቀበሌዎች ፕሮግራም በማውጣት ጉብኝት እያደረጉ፡፡ ከምርጫ ቦርድ አባላትን የመመልመል፣ ማደራጀት፣ ቢሮ የመክፈት ፍቃድ እንዳላቸው የሚገልፅ ሰነድ በእጃቸው እንደሚገኝ አሳይተው የተወሰዱባቸውን ንብረቶች ማስመለስ ቢችሉም ለሁለተኛ ጊዜ ይህ ችግር መፈጠሩን ሰብሳቢው ያስረዳሉ፡፡ ይህን እያደረጉ ያሉትም በታችኛው የመንግሥት መዋቅር ሥር የሚገኙ የቀበሌ አመራሮች መሆናቸውን ሰብሳቢው ይገልፃሉ፡፡ ይህ ሊሆን የቻለውም ኢዜማ ዜግነትን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ አደረጃጀትን የሚከተል ፓርቲ በመሆኑ የቀበሌው አመራሮች መሰል ድርጅት በቦታው ላይ እንዲንቀሳቀስ ፍላጎት ስለሌላቸው እንደሆነ ሰብሳቢው ያስረዳሉ፡፡ የተፈጠረውን ችግር በማስመልከትም ምስክሮችን አሟልቶ በማቅረብ ጉዳዩን በሕግ ለመፍታት በፖሊስ ጣቢያ ቃል ሰጥተው አስመስክረው ክስ መመስረታቸውን ሰብሳቢው ይናገራሉ፡፡ ገልፀዋል፡፡ ከምርጫ ወረዳው በዘለለ በየቀበሌውም ማስታወቂያው በምርጫ ወረዳው በተመረጡ አስመራጭ ኮሚቴ አማካኝነት በየማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ እንዲለጠፍ መደረጉን ሰብሳቢው ጠቁመዋል፡፡ በዚህም መሰረት 9 ሰው ማመልከቻ ማስገባት መቻሉን ሰብሳቢው አስረድተዋል፡፡

### እንደ መውጫ

የጉፋ ምርጫ ወረዳ ነዋሪዎች በመልካም አስተዳደር እጦት፣ በሥራ አጥነትና ሥር በሰደደ የኢኮኖሚ ችግር የተነሳ ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ እንደሚመሩ የምርጫ ወረዳው ሰብሳቢ ይናገራሉ፡፡ እነዚህን የአካባቢው ነዋሪዎች መሰረታዊ ችግሮች ለመቅረፍም እንደሚያልሙና ለዛም እየተንቀሳቀሱ እንዳለ

> ‹‹ሕብረተሰቡን ሰላም እየነሱት ያሉት የመልካም አስተዳደር እጦትን መቅረፍ፣ የወጣት ሥራ አጥነት ችግር እልባት መስጠት፣ ሕዝብን ያላማከለው ልማትን ዜጎችን በሚያማክልና ተጠቃሚ በሚያደርጉ መልኩ መቅረፅ እንዲሁም የአካባቢው ነዋሪ በመረጠውና በፈለገው ሰው የመተዳደር መብቱ እንዲጠበቅለት እንደሚሠሩ ሰብሳቢው ይገልፃሉ፡፡››

ቀበሌዎቹ ምን እየሠሩ እንዳለ የክትትል ሥራ እየተሠራ እንዳለ ሰብሳቢውአስረድተዋል፡፡ የምርጫ ወረዳው ጠንካራ ጎን የሚሉትም ይህን አደረጃጀቱን መሆኑን የሚያወሱት ሰብሳቢው መልካም ሥራ ቢሠራም ብዙ ሥራ እንደሚቀር ያስረዳሉ፡፡ በምርጫ ወረዳቸው ነዋሪ ከሆነው ሕዝብ ውስጥ ቢያንስ 80 በመቶውን የኢዜማ አባል እና ደጋፊ ለማድረግ አቅደው መነሳታቸውንና ያንንም ለማሳካት በሴል ደረጃአ ባላትን በማደራጀት እቅዳቸውን ለማሳካት ጥረት እያደረጉ እንደሚገኙ ይገልፃሉ፡፡

### በአደረጃጀት ጊዜ የገጠማቸው ፈተና ምን ይመስላል?

በአደረጃጀት ጊዜ ከቀበሌ አመራሮች በኩል የፓርቲው ሰነድ የሆኑትየ ፓርቲው ፕሮግራም፣ ደንብና ሕጋዊ ደረሰኝ ተወስዶባቸው እንደነበር ይገልፃሉ፡ ሆኖም በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት ፍርድ ቤቶች ዝግ ስለሆኑ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አለመቻሉን ሰብሳቢው ገልፀዋል፡፡ እነዚህ ዓይነት መሰልመሰናክሎች እየፈጠሩ ያሉትም በመንግሥት ታችኛው መዋቅር ሥር የሚገኙ የቀበሌ አመራሮች መሆናቸውን ከሰብሳቢው ለመረዳት ችለናል፡፡

### የወረዳው አስመራጭ ኮሚቴ ኢዜማን ወክለው የሚወዳደሩ እጩዎችን ማግኘት ችሏል?

ከማዕከል አስመራጭ ኮሚቴ በምርጫ ወረዳው እንዲመረጥ መመሪያ ከተላለፈ በኋላ መመሪያውን በመጠበቅ 5 አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ እንዲመረጥ መደረጉንና ኢዜማን ወክለው ምርጫ ለመወዳደር የሚፈልጉና የወጣውን መመሪያ የሚያሟሉ አመልካቾች ማመልከቻቸውን እንዲያስገቡ መደረጋቸውን ሰብሳቢው

ሰብሳቢው ይገልፃሉ፡፡ በምርጫ ወረዳቸው አሸናፊ ሆነው ከወጡም ሕብረተሰቡን ሰላም እየነሱት ያሉት የመልካም አስተዳደር እጦትን መቅረፍ፣ የወጣት ሥራ አጥነት ችግር እልባት መስጠት፣ ሕዝብን ያላማከለው ልማትን ዜጎችን በሚያማክልና ተጠቃሚ በሚያደርጉ መልኩ መቅረፅ እንዲሁም የአካባቢው ነዋሪ በመረጠውና በፈለገው ሰው የመተዳደር መብቱ እንዲጠበቅለት እንደሚሠሩ ሰብሳቢው ይገልፃሉ፡፡

# < <የፖለቲካ ልዩነት አሁን አያስፈልግም፤መንግሥት እርዳታ ያስፈልገኛል በሚልባቸው ቦታዎች ሁላ ኢዜማ በሚችለው አቅም እርዳታ ለማድረግ ዝግጁ ነው> >አበበ አካሉ የኢዜማ ዋና ጸሐፊ

መጋቢት 26 ቀን 2012 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት እገዛ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተቋቋመው የኮሮና ቫይረስ መከላከል ብሔራዊ ግብረ ኃይል ኮሚቴ አስታወቀ፡፡ ፓርቲው መጋቢት 22 ቀን 2012 ዓ.ም ለብሔራዊ ግብረ ኃይል ኮሚቴ ሰብሳቢ በጻፈው ደብዳቤ ወረርሽኙን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት በሚችለው አቅም ሁሉ ለማገዝ ቁርጠኝነቱ እንዳለው ገልጿል፡፡ የፓርቲው መዋቅር ባሉባቸው ወረዳዎች ሥር የሚገኙ አባላቱ ወረርሽኙን ለመከላከል በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት እንዳላቸው ለፓርቲው አመራሮች በመግለፅ ላይ እንደሚገኙ ፓርቲው በዚሁ ደብዳቤው ላይ ገልጿል፡፡ ሀገራዊ ኮሚቴው የሚሰጠው መመሪያ ካለም ኢዜማ መመሪያውን ለመቀበል ዝግጁ እንደሆነና በኢዜማ ስር ያሉ በሙያቸው መሳተፍ የሚፈልጉ የሕክምና ባለሙያዎች እንዲሁም ሌሎች አባላት ወረርሽኙን ለመከላከል በሚደረገው ርብርብ መሳተፍ ስለሚፈልጉ ሀገራዊ ኮሚቴው የሚያስተላልፈው መመሪያ ካለ እሱን መመሪያ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኝ ፓርቲው ለብሔራዊ ግብረ ኃይል ኮሚቴው በላከው ደብዳቤ ላይ ጠቅሷል፡፡



እንዲህ ዓይነት አደጋን ለመቋቋም ሁሉም በግሉ ከሚያደርገው ጥንቃቄ ባሻገር በሀገር ደረጃ የሚወሰዱ የጥንቃቄና የመከላከል እርምጃዎች በተቀናበረ መልክና ከአንድ ማእከል በሚወርድ መመሪያ መደረጉ ትክክል ነው ብለን እናምናለን ያለው የኢዜማ ደብዳቤ ይህ አደጋ በሁሉም ዜጋ ላይ የመጣ እንደመሆኑ መጠን ዜጎችን በተደራጀ መልኩ በመከላከሉ ሂደትና በበሽታው ምክንያት በሀገር ላይ የሚመጣውን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጫና ለመቋቋም ማሳተፍ የተቀላጠፈ ውጤት ለማምጣት ተገቢና እጅግ አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን ሲል ለብሔራዊ ግብረ ኃይሉ ደብዳቤ የጻፈበትን ምክንያት አብራርቷል።

ዜጎች መድረክ የኢዜማ ዋና ጸሐፊ የሆኑትን አበበ አካሉን ፓርቲያቸው ለብሔራዊ ግበረ ኃይሉ የላከውን ደብዳቤ በማስመልከት አነጋግሯቸው የነበረ ሲሆን ዋና ጸሐፊው በዚህ ፈታኝ ወቅት እርስ በእርስ መተባበር ግድ እንደሚል አስረድተዋል፡፡ኃያላን ሀገራት እንኳ ምን ያሕል እንደተቸገሩ እየተመለከትን ነው ያሉት አበበ፣ የፖለቲካ ልዩነት አሁን እንደማያስፈልግ ገልፀው መንግሥት እርዳታ ያስፈልገኛል በሚልበት ቦታ ሁሉ ፓርቲያቸው በሚችለው አቅም እርዳታ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን አስረድተዋል፡ ፡የሚያስፈልገውን እርዳታ ለማድረግም በየወረዳው ያሉ የኢዜማ አመራሮች በተለይም የወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፣ የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ እና የሙያ ማኅበራት ቋሚ ኮሚቴ በጋራ የሚያስተባብሩት ኮሚቴ በየምርጫ ወረዳው እንደሚቋቋመው ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ ኮሚቴዎች በወረዳ ደረጃ ከሚዋቀሩ የመንግሥት አካላት ጋር በቅርበት እየሠሩ ድጋፍ ለሚያስፈልገው ሕዝብ ድጋፍ የማሰባሰብ ሥራ እንደያከናውኑ እንዲሁም በፓርቲው ውስጥ ያሉ የሕክምና ባለሙያዎችም የማማከርና አገልግሎት የመስጠት ሥራ እንዲሠሩ ፓርቲያቸው ውሳኔ ማስተላላፉና ዋና ፀሐፊው ገልፀዋል፡፡






የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)